# ቆንጆ የሁሉም ናት

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*



*አንደኛው አግኝቶ ውዴ ፍቅሬ ሲላት፤*

*ሌላው በማጣቱ ጧት ማታ ሲመኛት፤*

*የውበት ዕድምተኞች እያዩ ሲያደንቋት፤*

*ያላየው እያየ ውበቷን ሲጎመዠ፤*

*ምኞቱን ለማስመር ዐይኑ ሲንቀዠቀዠ፤*

*የሰማው ላልሰማ ዝናዋን ሲረጨው፤*

*በውበት ረሃብ ምራቁን ሲያስውጠው፤*

*ያገኛት ሲጨፍር ልቡ ጮቤ ሲረግጥ፤*

*በውበቷ ነዶ በውበቷ ሲቀልጥ፤*

*በምኞት ጧት ማታ ያጣት ሲቁነጠነጥ፤*

*አካሉ ሲፈላ ጨጓራው ሲመለጥ፤*

በድንገት ያያትም ሊደናቆት ሲቸራት፤

መቸ ያለ ምክንያት ቆንጆ አርጎ ፈጠራት ?!

ነው እንጂ እንዲያደንቃት፤

ሁሉም እንዲመኛት ::

የራሱን ተፈጥሮ የራሱን ማንነት፤

እንዲችል ለማየት፤

በቆንጆዋ ውበት፤

ከጥንቱ ሲፈጥራት፤

አረጋት መስታወት፤

ለራስ መመልከቻ እኔስ ማነኝነት ::

ስለዚህ፤

የሚታይ ተፈጥሮ የሚናፈቅ ውበት፤

እንዴት ተደብቆ ይቀራል ከማጀት ?!

ወቶ ባደባባይ መታየት አለበት፤

መደነቅ አለበት !!

እናም !

ቆንጆ የሁሉም ናት !

ማነው የሰስታም ያንድ ሰው ያረጋት ??!!

ለመላው ሴት ልጆች መታሰቢያ ትሁንልኝ ታኅሳስ 10 ቀን 2002 ዓ.ም. 19 /12/2009

ከስንኟ ቋጣሪ ሃሳብ መወራወር ለሚሹ በ asradew@live.fr ያገኙታል ::